# የቆሰለ ፖለቲካ - ምን ይዞ ጉዞ

ታሪኩ አባዳማ ነሐሴ 20002

ቁስል በግዜ ካልታከመ ያመረቅዛል ፣ ይሰፋል ፣ ለከፋ እና ለተባባሰ ስቃይ ይዳርጋል። ጦር ሜዳ ወታደር ሲቆስል የመጀመሪያው እርምጃ ቁስለኛውን ማግለል እና ተገቢ ህክምና እና ክብካቤ የሚያገኝበትን ፈጣን እርምጃ መውሰድ ነው። ቁስለኛ ወታደር ተሰልፎ ከጠላት ጋር ግብግብ መግጠም አይታሰብም። ደግሞም ወታደር ቆሰለ ተብሎ እንደ አሮጌ ቁና የሚወረወርበት ሁኔታ ዘላቂ ድል ከመጎናፀፍ አንፃር ሲታይ አደገኛ ነው። ቁስል ወቅታዊ ትኩረት እና ህክምና ይጠይቃል። የቆሰለ አካል ፣ የተቋሰለ መንፈስ ይዞ መጓዝ በማናቸውም ረገድ ለስኬት መብቃት እጅግ አጠያያቂ ነው።

አስተያየቴ ለብሔራዊ አንድነታችን ተሰልፈናል የሚሉትን ተቃዋሚ ሀይሎች የሚመለከት ነው። የፖለቲካ ሳይንስ ተማሪዎች ምን ብለው እንደሚጠሩት ባላውቅም የአገራችን ፖለቲካ በቁስል የተበከለ መሆኑን ሁላችንም የምንረዳው ይመስለኛል። ብዙ ዘመን ቆጥረናል ከሚሉት የፖለቲካ ድርጅቶች እስከ ቅርቦቹ ድረስ የምናየው እውነት ሁሉም ቁስለኛ መሆኑን ብቻ ነው - ያልተሸፈነ ፣ ያገጠጠ ቁስል። ዘመን ባለፈ መጠን ቁስላችንን ጠግገን ለትግል ከመሰለፍ ይልቅ ቁስሉን የምንወጋበት እንጨት ስናሾል ትግሉን ስናሽመደመድ እንገኛለን። የቆሰለ ፖለቲካ አንግበን ኢትዮጵያን ለመታደግ እንመኛለን።

ሁላችንም የወያኔ አገዛዝ ለአገር ዘላቂ ጥቅም አይበጅም እንላለን፤ ጎጠኝነት ብሔራዊ ጥቅም ይፃረራል ፣ አገራዊ የባለቤትነት ስሜት ይሸረሽራል ፣ ህዝብ ይከፋፍላል ፣ ያዳክማል እንላለን። በፅኑ ብሔራዊ ስሜት ላይ ያልተገነባ አገር - አገሩም አገር ህዝቡም የባለቤትነት ስሜት ያለው ህዝብ አይሆንም እንላለን። የተከፋፈለ እና የተዳከመ ህዝብ በቀላሉ ለጠላት ጥቃት ይጋለጣል ብሎም ለስግብግብ አምባገነን ገገርዎች ሰለባ ይሆናል እየተባለ ሲነገር ሲዘከር እዚህ ደርሰናል።

ቁስለኛ ፖለቲካችን ግን የዝንብ መጫወቻ አድርጎናል።

ወያኔ ኢትዮጵያን ቀናንሶ ሽራርፎም ቢሆን በመዳፉ ውስጥ አስገብቷል። ያሻውን ለማድረግ የሚያግደው አንዳችም ሃይል እንደሌለ ደጋግሞ በሚወስዳቸው እብሪት እና ንቀት የተመላባቸው እርምጃዎች አረጋግጧል። ያሻውን ገድሎ ፣ ያሻውን አስሮ ፣ ለአገዛዙ ዕድሜ መራዘም ይጠቅማል የሚለውን ማናቸውንም ፀረ-አገር ድንጋጌ አውጆ ፤ በየትኛውም ያገሪቱ ክልል ያሻውን መሬት ቆርሶ ለአገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች ሳይቀር ገፀ በረከት ሰጥቶ እየገዛን ነው።

ወያኔ እንደ መንግስት ፕሮቶኮል ፈርሞ ፣ እንደ ማጅራት መቺ አድብቶ የንፁሀን ዜጎች ደም አፍስሶ ፣ ዘርፎ ፤ እንደ ወመኔ ተቃወሚ በሚለው ላይ ለከት የሌለው ስድብ ለጥፎ ፣ አበሻቅጦ ፣ አዋክቦ ፣ ጎሽሞ ፣ አስሮ እና ገድሎ በአገዛዙ ቀጥሏል።

እኛ ቁስላችንን ማከም ተስኖን አገሪቱ የዝንብ መራቢያ ዱር ሆናለች።

ሃያ አመታት የጎጥ አገዛዝ አልበቃ ብሎን ዛሬም ቁስላችንን በሹል እንጨት እየወጋን ነው። አውጥተን አውርደን ፣ በጥልቀት ጉዳዮችን መርምረን ፣ ትርፍ እና ጉዳቱን በመጠን እና ግዜ አስልተን ፣ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት እና ድካም ገምተን የተግባር መመሪያ መቀየስ ከቶ አይሆንልንም። በግፊት እና የተጨናነቀ ሁኔታ ውስጥ በርብርቦሽ እና በዘመቻ ፣ በሆታ ጋጋታ ተፍ ተፍ በማለት ውጤት መጨበጥ እንመኛለን። የወያኔ ምርጫ ሲቃረብ ህብረት፣ ግንባር፣ ፊርማ እያልን እንራወጣለን - ያውም ከነቁስላችን።

ውጤት ቢገኝ ባይገኝ ፣ ያሰብነው ቢሳካ ባይሳካ በአመለካከታችን እና በዝንባሌአችን ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም። ያው እንደ ዛሬ ሰላሳ አመቱ ፣ ያው እንደ አምና ከቻምናው በቁስል የተበከለ መፈክራችን ፣ መዝሙራችን አይለወጥም።

ያመረቀዘው ቁስል ለጠላትም ለወዳጅም ገጥጦ ይታያል።

በተሳካ የግንባታ ሂደት ያለፉ ወይንም እየተጓዙ የሚገኙ አገራትን ታሪክ ልብ ብለን ብናጤን የምረዳው ካለ ፖለቲካዊ መፍትሔ ለመሻት አንደ ወቅቱ ሁኔታ ተስማሚ ስልት በግዜ መቀየስ ይጠይቃል። አሰላለፍ ይቀየራል ፣ ብሔራዊ ደህንነትን እና አገራዊ ብልፅግናን ያሰቀደመ አቋም ይቀረፃል። ይህ አገራዊ አጀንዳ ዳር እስኪደርስ ድረስ ድርጅታዊ እና ግላዊ አጀንዳ ይታቀባል። ስለሆነም በጠባብ ድርጅት ስሜት እርስ በርሱ እየተናከሰ ገዢውን ፀረ-አገር ሀይል ማስወገድ የሚታሰብ አይደለም። መናከስ ያቆስላል - እናም ቀዳሚው እርምጃ ተናካሽ ጥርሶች እንዲለዝቡ ፣ በንክሻ የቆሰለው መንፈስ እንዲጠግግ ማከም ነው።

ገዢዎች ባሻቸው መንገድ ከፋፍለው ፣ በስጋት እና ባለመተማመን መንፈስ አንገት አስደፍተው እንዲገዙን ዕድል የሚሰጣቸው ከሆነ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እና መሪዎቹ ለአገራችን ጥፋት ከጠላት ባላነሰ ደረጃ ተጠያቂ የማይሆኑበት ምክንያት የለም። የሰው ልጅ ያለፈውን እንደ ትምህርት ተሞክሮ ፣ መጭውን አውጥቶ አውርዶ በማቀድ ካነጣጠረው ግብ ለመድረስ በብልሀት እና ትዕግስት መጓዝ ይጠበቅበታል።

ቁስላችን አስቸኳይ (emergency) ህክምና ይሻል። ፖለቲከኞቻችን በጠረቤዛ ዙርያ ተቀምጠው ያመረቀዘውን ቁስል የሚሽሩበት ወቅት ቢረፍድም ዕድሉ ዛሬም አለ። ሌላ ዙር የወያኔ ምርጫ እና ግርግር መጠበቅ የሚሻ ጉዳይ አይደለም። የማያሻማ ግብ ላይ ያነጣጠረ ስልት ሊነድፉ ብቃቱም ችሎታውም እንዳላቸው ማስመስከር የሚችሉበት ወቅት አሁን ነው። የሚነድፉት እቅድ ሁለንታነዊ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ሁሉም የበኩሉን የሚልበት ግልፅ እና አሳታፊ መድረክ ሊመሠረቱ ይገባል። በሂደት የሚያጋጥመውን ፈተና ያገናዘበ ፣ የመጨረሻውን ውጤት በጉልህ ያስቀመጠ ራዕይ ሊያንፀባርቅ የሚችል ስምምነት መቅረፅ ይኖርባቸዋል። ፖለቲከኞች የዜጎች ድምፅ እና ፍላጎት የሚስተናገድበት ፣ የሚካተትበት ሀይል ለመፍጠር  በስፋት ሊሰሩ ይገባል። ቁስለኛው ታክሞ በሙሉ አካል ወደ ትግሉ ሜዳ የሚመለስበት ህክምና ለማድረግ ቀዶ ጥገና ይደረግ። ቁስሉ ፈጥኖ እንዲሽር - የውሻ ቁስል እንዲሆን ሁሉም በያለበት በፀሎትም በገንዘብም ድጋፍ ያድርግ።

ቁስለኛ ወታደር ሰብስቦ ክተት ቢያውጁ ማስፈራሪያ እንኳ አይሆንም።

የፖለቲካ ቁስል ለማከም ሁነኛ ዕውቀት ይጠይቃል። በየፓልቶኩ የፖለቲካ ቀዶ ጥገና ለማድረግ የሚደፍሩ የመንደር ሀኪሞች ለግዜውም ቢሆን እጃቸውን ቢሰበስቡ ለሁላችንም ይጠቅማል። የፖለቲካ ጥያቄ ያንድን አገር እና ህዝብ ህልውና የመኖር አለመኖር ጥያቄ የሚመረምር እና መፍትሔ የሚሻ ብርቱ ጉዳይ ነው። የጎለመሰ አይምሮ ፣ በንባብ እና በልምድ የተኮተኮተ እና የዳበረ ጭንቅላት ይጠይቃል። ጥልቀት ባለው መርሆ ላይ የተገነባ ውይይት ማድረግ ፣ መስጠት እና መቀበል ፤ ለመማር ዝግጁ መሆን በወግ እና ሥርዓት ሀሳብ ማንሸራሸር ግድ ይላል። በቀላሉ በተገኘ የፓልቶክ አይነት መድረክ እየተነሱ የፖለቲካ መሀንዲስ እኔ ነኝ ማለቱ ፣ የፖለቲካ ስልት መቀየሱ፣ ሰላማዊ ይሁን ወይስ አመፅ እያሉ ዝርዝር የትግል አቅጣጫ መቀየሱ እናም እንዱን አሞግሶ ሌላውን መዘርጠጡ ቁስሉን በእንጨት መውጋት እንጂ ጋት አያራምድም። የሚሠሩትን የሚያውቁ - የሚያውቁትን የሚሠሩ ብቻ ናቸው - ሌላው ከዝባዝነኬ አያልፍም።

እውነተኛ ፍላጎታችን ኢትዮጵያን መታደግ ከሆነ ለኢትዮጵያ ስንል ሁሉን እናድርግ። ይቅር የምነለው ካለ ከልባችን ይቅር እንበል ፣ የማይጥመን አቋም ካለ በሚፈጠረው ነፃ የመወያያ መድረክ ሰብሰብ ባለ መልኩ ሀሳባችንን በመቻቻል እና በመደማመጥ መንፈስ እናስተናግድ። ፖለቲካ የግል ሸቀጥ አገርም የጓሮ እርሻ አይደሉም፤ ፖለቲካን ግላዊ ጥላቻ ማነፀባረቂያ ወይም ነጮቹ እንደሚሉት (personal) አናድርገው።

እውነት እውነት እላችኋለሁ የቆሰለ ወታደር ለድል እንደማያበቃ ሁሉ የቆሰለ ፖለቲካ ለውጤት አያበቃም። ቁሰላችንን መሸፈን ብቻ ሳይሆን አክመን ለመፈወስ ብሎም ካሰብነው ግብ ለመድረስ እንዲቀናን የዞትር ፀሎቴ ነው።